መልእክት ሰባት

**የእግዚአብሔርን የልብ መሻት ለመፈጸም**
**እና በእግዚአብሔር ፊት ያለውን የሰውን ፍላጎት ለመሙላት**
**በብሉይ ኪዳን**
**እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር እና በሰዎች መካከል ያለው እንቅስቃሴውን በተመለከተ**
**እና በአዲስ ኪዳን**
**እግዚአብሔር በሰው ውስጥ ያለውን እንቅስቃሴውን በተመለከተ ያለው**
**ውስጠ-መሠረታዊው መለኮታዊ መገለጥ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል:- ኢዮብ 10፡13፤ 42፡1-6፤ ኤፌ. 3፡9፤ ዮሐ. 1፡1፣ 14፤
ማቴ. 1፡23፤ 2 ቆሮ. 3፡18፤ 4፡16-17፤ ሮሜ. 8፡29-30፤
ቆላ. 1፡12፣ 15-9፤ 3፡4፣ 10-11፤ ሐዋ. 26፡16-18፤ ኤፌ. 3፡16-19

1. **የእግዚአብሔር ከሰዎች ጋርና በሰዎች መካከል የሆነው እንቅስቃሴ ያለው በብሉይ ኪዳን ውስጥ ነው፤ የእግዚአብሔር ከሰዎች ጋርና በሰዎች መካከል እንቅስቃሴ ለክርስቶስ እና ለቤተ ክርስቲያን ዘላለማዊ ኢኮኖሚውን ለመፈጸም ቀጥተኛ እንቅስቃሴው ሳይሆን ለዘላለማዊ ኢኮኖሚው በአዲሱ ፍጥረት ውስጥ ላለው ቀጥተኛ እንቅስቃሴው ዝግጅት በአሮጌው ፍጥረት ውስጥ ያለው ቀጥተኛ ያልሆነው እንቅስቃሴው ነበር—2 ቆሮ. 5፡17፤ ገላ. 6፡15:-**
   - ሀ. በመልኩ በእግዚአብሔር እንደተፈጠረ ሰው፣ እግዚአብሔርን ይኖረው፣ ይገልጠው እና ይወክለው ዘንድ ሰው እግዚአብሔርን (በሕይወት ዛፍ የተመሰለው) እንደ ሕይወቱ መውሰድ ያስፈልገው ነበር፤ እንዲህ እንዳለው ማንነት፣ ወደ ከበሩ ዕቃዎች መለወጥና እንደ እግዚአብሔር አምሳያ መገንባት ያስፈልገው ነበር—ዘፍ. 1፡26-27፤ 2፡9-12፣ 18-24።
   - ለ. እንደ ወደቀ ሰው፣ በክርስቶስ ውስጥ (በመሥዋዕቱ የቁርበት ልብስ እንደተመሰለው) በእግዚአብሔር ይጸድቅ ዘንድ ሰው ለቤዛነቱ ክርስቶስን (ከፈሰሰው ደሙ ጋር በመሥዋዕቱ እንደተመሰለው) መቀበል ያስፈልገው ነበር፤ በተጨማሪም የወደቀው ሰው ከሰይጣን ከ"እባቡ" የሞት ኃይል ይድን ዘንድ ክርስቶስን እንደ ሴቲቱ ዘር መቀበል ያስፈልገው ነበር—3፡8-9፣ 15፣ 21፤ ዕብ. 2፡14።
   - ሐ. እግዚአብሔር ሰውን ተመለከተ እና በሚቃጠለው መሥዋዕት በሰው ደስ ተሰኝቶ ነበር፤ እንደሚቃጠለው መሥዋዕት እውነታ ክርስቶስ ለእርካታው እና ደስ ለመሰኘቱ ለእግዚአብሔር እንደሚያረካ መዓዛ ለእግዚአብሔር ፍጹም የሆነና ለእግዚአብሔር እርካታ የሆነ ኑሮ ኖረ—ዘፍ. 4፡4፤ 8፡20-22፤ ዘሌ. 1፡9፤ ኢሳ. 42፡1፤ ማቴ. 3፡17፤ 17፡5፤ 12፡18፤ ዮሐ. 5፡30፤ 6፡38፤ 7፡18፤ 8፡29፤ 14፡24፤ ተዛ. 2 ቆሮ. 2፡15፤ መኃ. 4፡10-16።
   - መ. እግዚአብሔር ለአብርሃም በዘሩ (በክርስቶስ) የምድር አሕዛብ ሁሉ እንደሚባረኩ ቃል ገባለት—ዘፍ. 22፡18፤ ገላ. 3፡8፣ 14፣ 16-17።
   - ሠ. በእግዚአብሔር እንደተመረጠ ሰው፣ ወደ እግዚአብሔር ውስጥ ይገባና እግዚአብሔር የሆነውን ሁሉ ከክርስቶስ ጋርና በክርስቶስ ውስጥ ይደሰት ዘንድ (ዘጸ. 25—ዘሌ. 27) ሰው የእግዚአብሔርን ጥሪ መቀበልና መመለስ (ዘፍ. 12፡1-4)፣ በክርስቶስ እንደሚቃጠለው መሥዋዕት በእግዚአብሔር ፊት መኖር (ቁ. 7፤ 13፡18፤ 22፡13)፣ ኃጢአተኛ እንደነበር እና ሕጉን ለመጠበቅ አቅም እንደሌለው ያውቅ ዘንድ በሕጉ መጋለጥ (ዘጸ. 19፡8፤ 21—20፡21) እና ክርስቶስን እንደ መገናኛው ድንኳን፣ እንደ ካህኑ እና እንደ መሥዋዕቶቹ በመውሰድ ከእግዚአብሔር ጋር መኖር ያስፈልገው ነበር።
   - ረ. ዘላን በሆነው የኢዮብ የኑሮ መንገድ (ኢዮብ 1፡3) እና ለልጆቹ የሚቃጠል መሥዋዕት ባቀረበበት መንገድ (ቁ. 5) መሠረት፣ ኢዮብና ባልንጀሮቹ ምናልባትም በአብርሃም ዘመን የኖሩ ይመስላል (ዘፍ. 22፡13)፤ በዚያን ጊዜ የሙሴ አራት መጽሐፍት ከሕጉ ጋር ገና አልተጻፈም ነበር:-
      1. ያለጥርጥር ኢዮብና ባልንጀሮቹ በቃል ከቀደሙት አባቶች አንዳንድ መገለጥ ተቀብለዋል፤ ነገር ግን ከቀደሙት አባቶቻቸው የተቀበሉት ሊደርስ የሚችለው ቢበዛ በአብርሃም ዘመን የነበረው የመገለጥ ደረጃ ድረስ ብቻ ነው።
      2. ስለዚህ፣ እግዚአብሔር ከሰው ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ባላቸው ክርክር ውስጥ፣ ከእግዚአብሔር ፍርድ እና እግዚአብሔር በሚቃጠለው መሥዋዕት በኩል ለሰው ካለው ትኩረት ያለፈ ሌላ መለኮታዊ መገለጥ እንደተቀበሉ የሚያመለክት ምንም ፍንጭ የለም።
      3. ኢዮብና ባልንጀሮቹ ስለ ክርስቶስ እና ስለ እግዚአብሔር መንፈስ የሚያመለክት ምንም ቃል አልተናገሩም፤ እነርሱ በመለኮታዊ መገለጥ የመጀመሪያ ደረጃ ውስጥ ነበሩ።
      4. ለኢዮብ በመገለጡ፣ እግዚአብሔር እንዲህ የሚል ይመስላል፣ "ኢዮብ፣ እኔ በእርግጥ ማን እንደሆንኩ አታውቅም፤ እኔ ወሰን-የለሽ መሆኔን አልተገነዘብከም፤ በተጨማሪም፣ እኔ ለአንተ ልስጥ የወጠንኩትን ማሰብ

(መገመት) አትችልም፤ ኢዮብ፣ አንተ የእኔ ክፍል ትሆን ዘንድ ራሴን ድሰታህ በማድረግ ራሴን ልሰጥህ ወጥኛለሁ፤ የራስህ የሆነ ግብረገባዊነት፣ ፍጹምት እና ቅንነት ያለህ በመሆንህ አልረካሁም፤ እኔ እንድኖርህ እፈልጋለሁ፤ ውጥኔ ራሴን ወደ አንተ ውስጥ ማካፈልና ከራሴ በቀር ሌላ ምንም ነገር አለመስጠት ነው።"

5. ስለዚህ፣ በእግዚአብሔር የተመረጡና የተዋጁ ሕዝቦች ኢዮብ እንዳደረገው ራሳቸውን እንደ ፍጹምነት፣ ቅንነት እና ግብረገባዊነት በሆኑ የሰው ሰናይ ባሕሪያት ራሳቸውን መገንባት አያስፈልጋቸውም፣ ነገር ግን ዋላ [ውኃ] እንደሚናፍቅ እግዚአብሔርን መፈለግና በእግዚአብሔር በዓላት ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር እግዚአብሔርን መደሰት ያስፈልጋቸዋል (መዝ. 42፡1-5፤ 43፡3-5) ይህም እነርሱ የደረሱበትንና ያገኙትን ሁሉ ለመተካት እግዚአብሔር ለእነርሱ ሁሉ ነገር መሆን ይችል ዘንድ ነው፤ ይህ ለኢዮብ ሦስቱ ባልንጀሮች፣ ለኤሊሁና ለኢዮብም እንኳን መልስ መሆን አለበት (ኢዮብ 10፡13፤ ተዛ. ኤፌ. 3፡9)።
6. በኢዮብ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ፣ ኢዮብ በስብዕና ሕይወቱ ያጠረው እግዚአብሔር ራሱ መሆኑን በማመልከት እግዚአብሔር መጣ፤ ከዚህ የተነሣ በእርግጥ የኢዮብ መጽሐፍ የተጠናቀቀ ፍጻሜ የለውም፣ [ፍጻሜው] እግዚአብሔርን በክርስቶስ እንደ እድል ፈንታው ይደሰት ዘንድ ከእግዚአብሔር ጋር እርሱን አንድ ለማድረግ እግዚአብሔር በክርስቶስ በኢዮብ በሙላት መገኘቱ (gain) መሆን የነበረበት፤ እንዲህ ያለው መገለጥ በሙላት የሚገኘው በአዲስ ኪዳን ብቻ ነው—40፡10-14፤ 42፡1-6፤ 10፡13፤ ተዛ. ኤፌ. 3፡9።

II. **በእግዚአብሔር ፊት የሰውን ፍላጎት ለማሟላት በሰው ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር እንቅስቃሴ ያለው በአዲስ ኪዳን ውስጥ ነው፤ በሰው ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር እንቅስቃሴ ከክርስቶስ የመጀመሪያ መምጣት እስከ በአዲስ ሰማይና በአዲስ ምድር የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም መገለጥ ድረስ ነው፤ ይህ እንቅስቃሴ በሰው ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ ነው—ዮሐ. 1፡1፣ 14፤ ኤፌ. 3፡16-19፤ ራእ. 21፡2፣ 9-10፡-**

ሀ. በእግዚአብሔር እንደተመረጠና እንደተጠራ ሰው፣ ሰው ሥጋ ወደ ለበሰውን አምላክ፣ ስለ እነርሱና ከእነርሱ ጋር የስብዕና ኑሮ ወደ ኖረው፣ ወደ ሞተው፣ ከሞት ወደ ተነሣው፣ ወደ ዐረገው እና እንደ እስትንፋሳዊው ክርስቶስ ሕይወትን-ሚሰጥ መንፈስ ወደሆነው ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ ማመን ያስፈልገዋል፣ ይህም እርሱ መዳናቸው፣ ሕይወታቸው እና ሁሉነገራቸው ይሆን ዘንድ ነው (ከማቴዎስ እስከ ሮሜ የተገለጠው)፡-

1. በድንግል ውስጥ ለመጸነስ እና ሰው ለመሆን ከእርሷ ለመወለድ፣ በዚህም መለኮትን ወደ ስብዕና ውስጥ በማምጣት፣ ሦስተኛ ንጥረ-ነገር ሳይፈጠር አምላክና ሰው እንደ አንድ አካል እንዲዋሐዱ በማድረግ እግዚአብሔር መጣ—ዘሌ. 2፡4-5፤ ዮሐ. 1፡1፣ 14፤ ማቴ. 1፡20፣ 23፤ 1 ጢሞ. 3፡16።
2. ኢየሱስ ሁሉንም ነገር በእግዚአብሔር ውስጥ፣ ከእግዚአብሔር ጋር እና ለእግዚአብሔር ያደረገበትን ኑሮ ኖረ፤ እግዚአብሔር በኑሮው ውስጥ ነበር፣ ከእግዚአብሔርም ጋር አንድ ነበር፤ ዱካዎቹን በመፈለግና በመከተል እንቀዳው ዘንድ በስብዕና ኑሮው የመከራ ሕይወቱን እንደ ሞዴል በፊታችን አስቀምጧል፤ ይህ እርሱንና ሕይወቱን ማስመሰልን አያመለክትም ነገር ግን እርሱ ራሱ በውስጥ እንደሚያድረው መንፈስ፣ ከሕይወቱ ብልጥግናዎች ሁሉ ጋር ራሱን በውስጣችን እንዲያራባ በመከራችን እርሱን እንደ ጸጋ ከመደሰት የሚመጣ የራሱን ርቢ ያመለክታል—ኤፌ. 4፡20-21፤ 1 ጴጥ. 2፡21።
3. ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ሥጋ እንደለበሰው ሦስታንዱ አምላክ እና እንደ ሦስታንዱ አምላክ አካል መልበስ (ቆላ. 2፡9)፣ አሉታዊ ነገሮችን ሁሉ ለማስወገድና ለእኛ ከውስጡ መለኮታዊውን ሕይወት ለመልቀቅ በስብዕናው የምትክነት እና ሁሉን-ያካተተ ሞት ሞተ (ሉቃ. 12፡49-51፤ ዮሐ. 12፡24)።
4. ሞትን ድል ነሣ፣ ሁሉን-አፍሪ (የሚያፈራ) ወደ ሆነ ትንሣኤ ውስጥ ገባ፣ የእግዚአብሔር በኩር ልጅ ሆኖ ተወለደ (ስብዕናን ወደ መለኮት ውስጥ በማምጣት) እና የክርስቶስን አካል ለማፍራትና ለማቀናበር ሕይወትን-የሚሰጥ መንፈስ ሆነ—ሐዋ. 2፡23-24፣ 32፤ 13፡33፤ ሮሜ. 1፡3-4፤ 8፡28-29፤ ዮሐ. 20፡22፤ 1 ቆሮ. 15፡45፤ 12፡13።
5. ወደ ሰማያት ሁሉን-የሚጥስ ዕርገት ፈጸመ እና ለመሰራጨቱና ለቤተክርስቲያን እንደ መንግሥቱ መገንባት (ሐዋ. 1፡8፤ 26፡16-18) ጌታ፣ ክርስቶስ፣ መሪ እና አዳኝ (መድኃኒት) ተደረገ (ሐዋ. 2፡36፤ 5፡31)።
6. በሞቱ፣ በትንሣኤውና በዕርገቱ አማኞችን ሁሉ ከራሱ ጋር አንድ አደረገ፤ ስለዚህ ሞቱ፣ ትንሣኤውና ዕርገቱ በሙሉ የእነርሱ ሆኗል፣ የእርሱ ልምምድም የእነርሱ ታሪክ ሆኗል—ሮሜ. 6፡5-6፤ ኤፌ. 2፡5-6፤ ከእንግሊዝኛው የዝሙር መጽሐፍ #949፣ ቁጥር 4።

ለ. ሕይወትን በሚያድለው መንፈስ ክርስቶስ ወደ ሆነው ነገር ይለወጥ ዘንድ፣ ሦስታንዱን አምላክ በክርስቶስ የሚገልጥ ሕይወታዊ አካል፣ የክርስቶስ አካል ለመሆን ከቅዱሳን ጋር ይገነባ ዘንድ፣ በሂደት ያለፈው ሦስታንዱ አምላክ ከከበረው ሦስት ክፍል ካለው ሰው ጋር መዋሐድ እንደሆነችው በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም መጠናቀቅ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ለማከናወን የእግዚአብሔር አዲስ ፍጥረት እንደሆነው አንዱ አዲሱ ሰው ይሆን ዘንድ፣ በዘላለም ውስጥ ብዙዎች የተካተቱበት የአምላክ-ሰው መገለጥ ይሆን ዘንድ፣ በክርስቶስ እንደሆነ አማኝ ሰው በክርስቶስ መለኮታዊ ሕይወት ማደግ ያስፈልገዋል (ከ 1ኛ ቆሮንቶስ እስከ ራእይ የተገለጠ)፡-

1. እግዚአብሔር በክርስቶስ ተቤዠን፣ ኃጢአታችንን ይቅር አለን፣ አጠበን፣ አጸደቀን እና ከራሱ ጋር አስታረቀን፤ እግዚአብሔር በክርስቶስ ውስጥ አስቀመጠን እርሱንም ጽድቃችን፣ ቅድስናችንና ቤዛነታችን አደረገው—ኤፌ. 1፡7፤ 1 ቆሮ. 6፡11፤ ሮሜ. 3፡22፤ 5፡10፤ 1 ቆሮ. 1፡30።
2. እግዚአብሔር በክርስቶስ ትንሣኤ በኩል ዳግም ወለደን፣ አሁን ያድሰናል፣ ይለውጠናል እና የክብር መልኩን ያስመስለናል (ቲቶ 3፡5፤ ሮሜ. 12፡2፤ ኤፌ. 4፡23፤ 2 ቆሮ. 4፡16፤ 3፡18፤ ሮሜ. 8፡28-30፤ ፊልጵ. 3፡21)።
3. በማደሱና በመለወጡ፣ በትንሣኤው እንድንለማመደውና ፍለጋ በሌለው ብልጥግናው እንድናተርፈው፣ ዘላለማዊ የክብር ብዛትን በሚሠራልን በመከራው ለመካፈላችን በሞቱ ውስጥ በማኖር፣ ይጨርሰናል—2 ቆሮ. 4፡16-18፣ 10፤ ፊልጵ. 3፡10፣ 8፤ ኤፌ. 3፡8።
4. እግዚአብሔር አብ በእግዚአብሔር ወልድ አካል ለብሷል (ቆላ. 2፡9)፣ እግዚአብሔር ወልድ እንደ እግዚአብሔር መንፈስ እውን ሆኗል፣ እና የሦስታንዱ አምላክ እውነታ ለመሆን እግዚአብሔር መንፈስ በእኛ ለማደር መጥቷል (ዮሐ. 14፡16-20)፤ አብ፣ ጌታና መንፈስ እንደ ሦስታንዱ አምላክ የክርስቶስ አካል ለሆነችው ቤተ ክርስቲያን ምንጭ፣ ንጥረ-ነገር እና ውስጠ-ነገር ሆኗል (ኤፌ. 4፡4-6)።
5. የሦስታንዱ አምላክ ምሥጢር በአማኞች ውስጥ ያለ እውነታ መሆኑን በተመለከተ፣ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ብዙ የሚነግራቸው ነገር ነበረው፣ ነገር ግን የእውነታ መንፈስ እነዚህን ነገሮች ለእነርሱ ለመግለጥ እስኪመጣ ድረስ ሊሸከሙት አልቻሉም ነበር (ዮሐ. 16፡12-15)፤ ይህ የተፈጸመው በእውነታ መንፈስ በዋናነት የእግዚአብሔርን ቃል፣ ማለትም፣ የእግዚአብሔር ምሥጢር ስለሆነው ክርስቶስ (ቆላ. 2፡2) እና የክርስቶስ ምሥጢር ስለሆነችው ቤተ ክርስቲያን (ኤፌ. 3፡4) በተመለከተ የሆነውን መለኮታዊው መገለጥ (ቆላ. 1፡25-27) ባጠናቀቀው በጳውሎስ በኩል ነበር።
6. ክርስቶስ በእግዚአብሔር ለቅዱሳን እንደ ተሰጠ መለኮታዊ ርስት እና በአማኞች ውስጥ እንዳለ ሕይወት፤ ሕይወታዊ አካሉ የሆነው የአዲሱ ሰው ብልቶች ሆኗል እንዲሁም በአዲሱ ሰው ብልቶች ሁሉ ውስጥ ነው፤ እግዚአብሔር ለእኛ፣ ለክርስቶስ አማኞች፣ የአምላክ አካል መልበስ የሆነውን ክርስቶስን ሁሉ ነገራችን ሊያደርገው ይፈልጋል—ቆላ. 1፡12፣ 15-19፤ 3፡4፣ 10-11፤ 1 ቆሮ. 12፡12-13።
7. ከእርሱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድና ከክብር ወደ ክብር ወደ ጌታ መልክ እንለወጥ ዘንድ፣ ራሱን እና የፈጸመውን፣ ያገኘውንና የደረሰበትን ሁሉ ለእኛ እውነታ ለማድረግ ሕይወትን እንደሚሰጠው መንፈስ በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ ልባችንን ወደ ጌታ በማዞር ራሳችን ጌታን ለማየት የጌታን ክብር ትኩር ብሎ መመልከትና ሌሎች እርሱን በእኛ በኩል ማየት እንዲችሉ የጌታን ክብር ማንጸባረቅ እንችላለን—2 ቆሮ. 3፡16-18።
8. እግዚአብሔር በክርስቶስ በእኛ ውስጥ ያለውን የመለወጥ ሥራ፣ መለወጡ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም፣ በመጀመሪያ በድል-ነሺዎቹ በሺሁ ዓመት መንግሥት (ራእ. 2፡7)፣ በመጨረሻም በሁሉም አማኞቹ በአዲሱ ሰማይና በአዲሱ ምድር እስኪጠናቀቅ ድረስ፣ የተመረጡትንና የተዋጁትን ሕዝቡ፣ ብዙዎች የተካተቱበት መገለጡ፣ የቱንም አይነት የሰዉ ሰናይ ባህሪ (ኢዮብ እንዳደረገው) ሳይሆን ለዘላለም (21፡1—22፡5) ራሱን በሙላት የሚገልጡ በማድረግ ያከናውናል።

© 2020 Living Stream Ministry